# ፊልጶስ ሐዋርያ

ስለ ሐዋርያው ፊልጶስ በሦስቱ በማቴዎስ በማርቆስና በሉቃስ ወንጌላት ከስሙ ብቻ በቀር የተመዘገበ የታሪክ ዝርዝር የለም ። በአራተኛው በዮሐንስ ወንጌል ግን ስለ ሐዋርያው ፊልጶስ አያሌ ዘገባዎች ይገኛሉ ።

የሐዋርያው ፊልጶስ ታሪክ ከዲያቆኑ ፊልጶስ ታሪክ ጋር ይማታል ። ምክንያቱም ከሐዋርያው ይልቅ የዲያቆኑ ፊልጶስ ሐዋርያዊ ተግባር በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ጐላ ብሎ ስለሚገኝ ይመስላል ። ከዚህም ጋር ዲያቆኑ ፊልጶስ ፦ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊዎች "ሐዋርያ" በመባል ስለተጠራ ነው ።

ተርቱልያኖስ ስለ ጥምቀት በጻፈው መጽሐፍ ክፍል 18 ላይ "መንፈስ ቅዱስ ሐዋርያው ፊልጶስን ከኢትዮጵያዊው ጀንደረባ ፊት ወሰደው" በማለት ተናግሯል ።

እንደ ተርቱልያኖስ አስተሳሰብ በሐዋርያት ሥራ 8 ፡ 1 - 40 አሥራ ሁለት ጊዜ ያህል የተጠቀሰው ፊልጶስ ሐዋርያው መሆኑ ነው ። ነገር ግን ይህ ታሪክ ከእስጢፋኖስና ከማኅበረ እስጢፋኖስ ጋር የተያያዘ ስለሆነ በሐዋርያት ሥራ 8 የሚገኘው ፊልጶስ ፣ ከሰባቱ ዲያቆናት አንዱ እንደ ሆነ ብዙዎች ሊቃውንት ይስማማሉ ።

ታሪክ ጸሐፊው አውሳብዮስ ደግሞ በሐዋርያት ሥራ 21 ፡ 8 ላይ ከሰብአቱ ዲያቆናት አንዱ ወንጌላዊ ፊልጶስ" በመባል የተጠቀሰው ሐዋርያው ፊልጶስ እንደ ሆነ በጻፈው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ክፍል 3 ምዕራፍ 31 ቁጥር 5 ላይ ጽፎአል ።

ይህ አስተያየት ሐዋርያም ዲያቆንም የሚባለው አንድ ፊልጶስ እንደሆነ ያመለክታል ሆኖም በብዙዎች የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ዘንድ በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ሁለት ፊል ጶሶች እንዳሉ ይታመናል ። እነዚህም ሐዋርያውና ዲያቆኑ ናቸው ።

አጠራጣሪ የሆነው ታሪክ ይቆይና አራተኛው ወንጌልና ትውፊት ስለ ሐዋርያው ፊልጶስ የሚናገሩትን መመልከት ይጠቅማል ።

ሐዋርያው ፊልጶስ ከጴጥሮስና ከእንድርያስ ከተማ ከቤተ ሳይዳ ነበረ (ዮሐ. 1. 44) ከቤተ ሳይዳ በመሆኑም ዓሣ አጥማጅ እንደነበረ ይነገራል ። እንደ ዮሐንስ የታሪክ አቀራረብ "ና ተከተለኝ" የሚለውን የጥሪ ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ የተቀበለ ሐዋርያው ፊልጶስ ነው ። ፊልጶስ ከተጠራ በኋላ በአራት የተለያዩ ሥራዎች ምክንያት በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ አራት ጊዜ ተጠቅሶ ይገኛል ።

፩. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጥሪ ከደረሰው በኋላ የፊልጶስ ተግባሩ ናትናኤልን ጠርቶ ከጌታ ጋር ማስተዋወቅ ነበር ። ናትናኤል "ከናዝሬት ደግ ሰው ሊወጣ ይችላልን" በማለት ስለ ክርስቶስ በተጠራጠረ ጊዜ የፊልጶስ መልስ 'ና - እና እይ' የሚል ብቻ ነበር ። ይህም ርሱ ራሱ ክርስቶስን በማየት እምነቱን እንደ አረጋገጠ ከማሳየቱ ጋር በክርክር ብቻ ሰውን ማሳመን የማይቻል መሆኑን ያመለክታል ።

ፊልጶስ ምሁረ ኦሪት እንደነበረ "ሙሴ በሕግ ነቢያትም ስለ እርሱ የጻፉትን -- የናዝሬቱ ኢየሱስን አግኝተነዋል" በማለት ለናትናኤል በመሰበኩ መረዳት ይቻላል ።

፪. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምስት እንጀራና ሁለት ዓሣዎችን አበርክቶ ከሴቶችና ከሕጻናት ሌላ ለአምስት ሺህ ሰዎች ከመመገቡ በፊት ፊልጶስ እንጀራ እንዲገዛ ተጠይቆ ነበር (ዮሐ. 6 ፡ 5 - 7) ። በዚህ ጥያቄ መሠረት ፊልጶስ የምግብ ግዥ ኃላፊ የነበረ ይመስላል ነገር ግን ፊልጶስ የሕዝቡን ብዛት ተመልክቶ "የሁለት መቶ ዲናር እንጀራ ቢገዛ እንኳ አይበቃቸውም" ሲል ለቀረበለት ጥያቄ መልስ ሰጠ ።

በዚያ ጊዜ አንድ ዲናር አሥራ ሁለት የስንዴ እንጀራ ወይም ሠላሳ ስድስት የገብስ እንጀራ ይገዛ ነበር ። በዚህ ረገድ የሁለት መቶ ዲናር እንጀራ ለአምስት ሺህ ሰዎች ይበቃ ኖሯል ። ግን ፊልጶስ ሴቶችንና ሕጻናትን ደምሮ በመቆጠር ለእያንዳንዳቸውም አንዳንድ እንጀራ እንደሚያስፈልጋቸው በመገመት የተጠቀሰው ገንዘብ እንደማይበቃ ተናገረ ።

ከዚህም ሌላ የሁለት መቶ ዲናር እንጀራ ከተገዛ በኋላ ሳይበቃ ቢቀር ጌታ ሊሞላበት እንደሚችል ፊልጶስ የተገነዘበ አይመስልም ። ሆኖም የክርስቶስ ተአምር በአምስት እንጀራና በሁለት ዓሣዎች ምክንያት ይገለጥ ዘንድ ስላለው ይህ ሆነ እንጂ ፊልጶስ ለክርስቶስ ጥያቄ ተቃዋሚ አልነበረም ።

፫. ፊልጶስ ለሦስተኛ ጊዜ በፋሲካ በዓል ዕለት ወደ ኢየሩሳሌም ከመጡት የግሪክ ሰዎች ጋር ይታያል ። ግሪካውያን በበዓሉ ላይ ክርስቶስን ለማየት በፈለጉ ጊዜ ፊልጶስ አገናኝ እንዲሆናቸው ጠየቁት ፤ ምክንያቱም ፊልጶስ የሚለው ስም የግሪክ ቃል በመሆኑ የሀገር ሰው የፈለጉ ይመስላል ። ሆኖም ፊልጶስ ለብቻው ሳይሆን ከእንድርያስ ጋር ሆኖ ወደ ጌታ አቀረባቸው (ዮሐ. 12 ፡ 20 - 22) ። ከዚህ ላይ ፊልጶስ ከጓደኛው እንድርያስ ጋር ሰዎችን ወደ ክርስቶስ በማቅረብ ሐዋርያዊ ተግባሩን ሲፈጽም ይታያል ።

፬. ፊልጶስ ለመጨረሻ ጊዜ ክርስቶስ የፋሲካን እራት በበላበት በላይ ቤት ውስጥ ረዥም ንግግር ሲያደርግ አንድ ጥያቄ በማቅረብ ተጠቅሶአል ። ጥያቄውም "ጌታሆይ አብን አሳየንና ይበቃናል" የሚል ሲሆን የተሰጠውም መልስ "አንተ ፊልጶስ ይህን ያህል ዘመን ከእናንተ ጋር ስኖር አታውቀኝምን? እኔን ያየ አብን አይቷል እንዴትስ አንተ አብን አሳየን ትላለህ ? እኔ በአብ እንዳለሁ፥ አብም በእኔ እንዳለ አታምንምን ? የሚል ነበር ።

ወደ ገጽ ፰ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# ፊልጶስ ሐዋርያ

ከገጽ ፩ የዞረ

እንግዲህ ሐዲስ ኪዳን ስለ ሐዋርያው ፊልጶስ የሚያስረዳው ይህ ከዚህ በላይ የተዘረዘረው ሲሆን ትውፊት ደግሞ ስለርሱ እንደሚከተለው ይናገራል ።

የእስክንድርያው ቀሌምንጦስ "ሚስቀላኒስ" በተባለው መጽሐፉ 3 ፡ 4 ላይ የክርስቶስ ጥሪ በደረሰው ጊዜ "በቅድሚያ ሊሂድና አባቴን እቀብር ዘንድ ፍቀድልኝ" ሲል የጠየቀው ሰው ሐዋርያው ፊልጶስ እንደሆነ ጽፎአል ። ግን ይህ ታሪክ በዚያ ጊዜም ሆነ ዛሬ በብዙዎች ሊቃውንት ዘንድ ተቀባይነትን ያገኘ አይመስልም ። ምክንያቱም ፊልጶስ በመጀመሪያ ጥሪ ከደረሳቸው ደቀ መዛሙርት አንዱ ሲሆን "አባቴን እንድቀብር ይፈቀድልኝ" ያለው ሰው ግን ከሐዋርያት ጥሪ በኋላ የመጣ ሰው በመሆኑ ነው (ሉቃ. 9 ፡ 59)

ስለ ፊልጶስ የተጻፈው ገድል እንደ ሚያስረዳ ፊልጶስ ወደ አቴና ሄዶ አስተምሮአል በሚያስተምርበትም ጊዜ 300 የአቴና ፈላስፋዎች እንደ ተቃወሙት በመጨረሻም ወደ ኢየሩሳሌም ተላልከው አናንያስ የተባለውን ሊቀ ካህናት አስመጥተው እንደ ተከራከሩት ይኸው ገድል ያስረዳል ።

ፊልጶስ ሊቀ ካህናት አናንያስን በተአምራት እንዲሞት ባደረገ ጊዜ አምስት መቶ የሚሆኑ አይሁድ አምነው ተጠመቁ ይላል ገድሉ ።

ትውፊት ፊልጶስ ወደ ብዙ ሀገሮች ወደ ሊድያ ወደ ፑርሺያና ወደ ጉል ወደ አፍሪቃም እንደ ሄደ ይናገራል ። ነገር ግን አውሳብዮስ በታሪክ መጽሐፉ 3 ፡ 21 ላይ እንደ ገለጠው ፊልጶስ በእስያ ውስጥ ሂራጶሊስ በተባለች ሀገር ሲያስተምር ሰዎች በጠላትነት ተነሥተው እንደገረፉት በጦር እንደወጉትና እንደሰቀሉት ይተርካል ። ፊልጶስ ከመሞቱ በፊት ሬሳው በበፍታ (በናይሎን) ጨርቅ እንዳይገነዝ ግን በፓፒሮስ (በዳውጃ) እንዲገነዝ ለደቀመዛሙርቱ ስለነገራቸው በዳውጃ ተገንዞ ተቀብሯል ። ይህም ክርስቶስ በተገነዘበት የጨርቅ አይነት ላለመገነዝ ስለፈቀደ ነው ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሕዳር 18 ቀን የዚህን ታላቅ ሐዋርያ በዓል በመንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት ታከብራለች ። ሕዳር 18 ቀን ያረፈበት ዕለት ነው ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያው ፊልጶስ ከዲያቆኑ ፊልጶስ የተለየ መሆኑን ለይታ ታስተምራለች በሐዋርያው ፊልጶስ ጸሎትና አማላጅነትም ተጠብቃ እንደምትኖር ታምናለች ።

ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ



www.ethiopianorthodox.org